በዋናው ውሣኔ ውሉ ፈርሶ ቦታው ለአመልካች እንዲመለስ የተወሰነ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ማዘጋጃ ቤቱ ቦታውን ለተጠሪዎች የሰጠ በመሆኑ ፍርዱ ሊፈፀም የሚችል አይደለም፡፡

በዚህም ምክንያት የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት የሰጠውን ምክንያት በመቀየር ውሣኔውን አጽንተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 10962 በታህሳስ 5 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

<u>ተ ጨ ማ ሪ   ት ዕ ዛ ዝ</u>

ይህ ችሎት ነሐሴ 14/1999 የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ



የሰ/መ/ቁ. 29371

ታህሣሥ 1 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካቾች፡-** 1. ሶፊያ መሐመድ ቀረበች፡፡
2. ከድጃ መሐመድ ቀረበች፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. ኢብራሂም መሐመድ
2. ፋጡማ መሐመድ } ጠበቃ ዘላለም ባይህ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ መሠረቱ የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም በአፈፃፀም ደረጃ ላይ ያለ ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ለአፈፃፀሙ መሠረት የሆነው ውሣኔ የተሰጠው ተጠሪዎች ወንድማቸው በሆነው አብዱልቃድር መሐመድ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ ተጠሪዎች በአማራ ብ/ክ/መ/የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተከሣሽ ይዞት የሚገኘው ከአባታቸው የተገኘውን የውርስ ሃብት እንዲያካፍላቸው የጠየቁ ሲሆን፣ ተከሣሹም ክሱን አምኖ በመቀበሉ ንብረቱ ተከራካሪዎቹን ጨምሮ ለሰባት /7/ የሟች ልጆች እኩል ይካፈል በማለት ፍ/ቤቱ ወስኖአል፡፡ በመቀጠልም ውሣኔን በስሩ የሚገኘው ባቲ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም ተጠሪዎችንና አብዱልቃድር መሐመድን /የሥር ተከሣሽን/ ብቻ በማከራከር በባቲ ከተማ የሚገኙ አራት ቤቶች እና አንድ መኪና ለተጠሪዎች እንዲሰጡ በማለት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካቾች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም

እና እንደዋናው ውሣኔ አባባል ይፈጸም ዘንድ እንዲታዘዝላቸው በመጠየቅ ለወረዳው ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ግን ቀደም ሲል የሰጠውን ትዕዛዝ አልለወጠም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መዝገቡ በጣም የቆየ በመሆኑና ለአፈጻጸምም ስላስቸገረ ለከፍተኛው ፍ/ቤት መቅረብ አለበት በማለት ትዕዛዝ ስለሰጠ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን መነሻ በማድረግ ጉዳዩን አይቶአል፡፡ በመጨረሻም የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በማሻሻል ንብረቱ በዋናው ውሣኔ መሠረት ሰባቱም ወራሾች እኩል ይካፈሉት በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪዎች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ የታየ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ /ትዕዛዝ/ በመሻር ቀደም ሲል በባቲ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠውን የንብረት ክፍፍል ትዕዛዝ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካቾች መጋቢት 5 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በዋናው ፍርድ ከተሰጠው ውሣኔ በተለይ ሁኔታ የተከናወነውን አፈፃፀም ተፈጽሞ ያለቀ ነው በሚል ብቻ አመልካቾች ዋናውን ፍርድ መሠረት አድርገው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪ ሆኖ የቀረበው እና በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ አፈፃፀሙ ተከናወነ የተባለው በዋናው ፍርድ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነው፡፡ በአማራ ብ/ክ/መ/የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ግልጽ ነው፡፡ በውርስ ተገኘ የተባለው ንብረት የሟች ወራሾች የሆኑት ሰባት ሰዎች እኩል ይካፈሉት የሚል ነው፡፡ ከሰባቱ ወራሾች መካከልም የአሁኖቹ



አመልካቾች ይገኛሉ፡፡ የባቲ ወረዳ ፍ/ቤት በከፍተኛው ፍ/ቤት የታዘዘውም /የተወከለው/ በዚህ መልክ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ንብረቶቹን ለወራሾች እንዲያከፋፍል ነው፡፡ እንዳየነው ግን ንብረቶቹን ለሁሉም ወራሾች እንዲከፋፈሉ አላደረገም፡፡ የተገኙት ንብረቶች እንዳሉ በቀጥታ ለተጠሪዎች ብቻ እንዲሰጡ ነው ያደረገው፡፡ ይህ አካሄድ በግልጽ የሚያሳየው አመልካቾች እና ሌሎቹ ወራሾች በውሣኔ ጭምር ያገኙትን የወራሽነት መብት እንዲያጡ መደረጋቸውን ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም አመልካቾች ትዕዛዝ እንዲታረምና እነሱም ድርሻውን እንዲያገኙ እንዲታዘዝላቸው ፍ/ቤቱን የጠየቁ ቢሆንም፣ ፍ/ቤቱ ተጨማሪ እርምጃ አልወሰደም፡፡ በእርግጥ ጉዳዩ ዋናውን ውሣኔ በሰጠው ከፍተኛ ፍ/ቤት እልባት ማግኘት አለበት በማለት የወረዳው ፍ/ቤት ለከፍተኛው ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሊያርም የቻለውም ይህን መሠረት በማድረግ ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 374/1/ ይመለከቷል/፡፡ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ትዕዛዝ የሻረው ደግሞ አፈፃፀሙ ከመጠናቀቁም በላይ፤ የትዕዛዙም አሰጣጥ ስነ-ስርዓትን የተከተለ አይደለም በማለት ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ክርክሩ እልባት ሊያገኝ የሚገባው በዚህ መልክ ሳይሆን፣ ቀደም ሲል እንዳመለከትነው በዋናው ውሣኔ መሠረት ተፈጽሞአል ወይስ አልተፈጸመም የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ነው፡፡ በዋናው ውሣኔ መሠረት የተከናወነ አፈፃፀም እንደሌለ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም እንደተገነዘበ በውሣኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ በእርግጥ እኛም እንደተገነዘብነው የከፍተኛው ፍ/ቤት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ለማረም የተከተለው አካሄድ ትክክል አልነበረም፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ ይህን አካሄድ ትክክል አይደለም በማለት የሰጠው ትችትም ስህተት ነው የምንለው አይደለም፡፡ ትክክል ሆኖ ያላገኘነው ሁለቱም ፍ/ቤቶች ዋናው ውሣኔ ሊፈጸም የሚችልበትን መንገድ አለማመቻቸታቸው